# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕብረት ስለሚመሰርቱበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 23/2012

# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕብረት ስለሚመሰርቱበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 15 (3) እና አንቀጽ 55 (2) እንዲሁም በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 34 መሰረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ህብረት መመሪያ ቁጥር 23/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሠጥ ካልሆነ በስተቀር፤

1. "አዋጅ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ነው፡፡
2. "ደንብ" ማለት የበጎ አድራጐት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባ እና አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 ነው፡፡
3. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፡፡
4. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የህብረቱ መስራች አባላትና በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን በአባልነት ያቀፈ የህብረቱ የበላይ አካል ነው፡ ፡
5. "የሥራ አመራር ቦርድ ማለት በህብረቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥና የህብረቱን እንቅስቃሴ በቅርበት የሚከታተል አካል ማለት ነው፡፡
6. በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በደንቡ አንቀጽ 34 የተሠጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

7. "ህብረት" ማለት በኤጀንሲው ወይም ስልጣን ካለው የክልል መንግስት መዝጋቢ አካል ህጋዊ ሰውነት ያላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የጋራ ሥራቸውንና አላማቸውን እንዲያስተባብር፤ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) ሥር የተዘረዘሩ ተግባራትን ለማከናወን በበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ የበላይ አካል ውሳኔ የሚቋቋም ራሱን የቻለ ተቋም ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት

1. ይህ መመሪያ በኤጀንሲው የሥልጣን ወሰን መሰረት ተመዝግበውና ህጋዊ ሰውነት አግኝተው በሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ህብረቶች ላይ ተፈጻሚ ነው፡፡
2. መመሪያው ህብረት ባልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 5. ህብረቶች ስለሚመሰረቱበት ዓላማዎች

1. ህብረቶች የሚመሰረቱት የአባል በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን ሥራና አላማቸውን ለማስተባበር መሆን ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ህብረቶች አባል የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር የማይቃረኑ የሚከተሉትን ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ፡፡

    ሀ) ለጋራ ግቦች ስኬታማነት አባሎቻቸውን መደገፍ፣

    ለ) የሀሳብ፣የመረጃ እና  የልምድ ልውውጥን ማካሄድ፣

    ሐ) የአባላትን አቅም የመገንባት ተግባራትን ማከናወን፣

    መ) የአባላትን ሥነ ምግባርና የሙያ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን መስራት እና ተመሳሳይ ተግባራት፣

    ሠ) የህብረቱ አባላት አላማቸውን ለማሳካት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በመፍታት፣ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይሰራሉ፡፡

3. ማንኛውም ህብረት ከላይ ከተመለከቱት ዓላማዎች ውጭ እንደ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የበጎ አድራጎት ሥራዎችን የማከናወን እንቅስቃሴ ውስጥ በቀጥታ መሳተፍ አይችሉም፡፡

## 6. ህብረት ለመመስረት የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች

በአዋጁና በደንቡ ላይ የበጎ አድራጎት ወይም ማህበር ለማቋቋም የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ህብረት ለመመስረት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. በህብረቱ መስራች አባላት የተፈረመ መተዳደሪያ ደንብ፣
2. ህብረቱን ለመመስረት መስራች አባላት የተስማሙበት ቃለ ጉባዔ፣
3. ከኤጀንሲው ወይም ስልጣን ካለው የክልል መዝጋቢ አካል የተሰጠና የታደሰ የምዝገባ ሰርተፊኬት፣
4. እያንዳንዱ የህብረቱ አባል በየራሱ የበላይ አካል ህብረቱን ለመመስረት ወይም የህብረቱ አባል ለመሆን ውሳኔ ያስተላለፈበት ቃለ ጉባዔ፣

## 7. የህብረት መተዳደሪያ ደንብ መያዝ ስለሚገባቸው ፍሬ ነገሮች

በአዋጁ አንቀጽ 68 እና በደንቡ አንቀጽ 6 ላይ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ መያዝ ያለባቸው አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የህብረት መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉት በተጨማሪነት መያዝ ይኖርበታል፡፡

1. አባላትን የሚቀበልበት ሥርዓት፤
2. ስለ አባላቱ መብትና ግዴታዎች፤
3. አባልነት ስለሚቋረጥበት ሁኔታዎች፤
4. የጠቅላላ ጉባዔው ድምጽ አሰጣጥና የሥብሰባ ሥነ ሥርዓት፤
5. ¾ጠቅላላ ጉባዔ የU`Ý“ ¾¨<d’@ ›W×Ø Y’ Y`¯ƒ
6. አባላት ስለሚያዋጡት መዋጮ፤
7. ህብረቱ ስለሚፈርስበት ሁኔታ፤

## 8. የህብረት አደረጃጀትና አባልነት

1. በአዋጁ አንቀጽ 57-63 ስለ ማህበራት የተደነገጉት እንደ አግባብነቱ ለህብረቶችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ህብረት ጠቅላላ ጉባዔ፣የሥራ አመራር ቦርድና ኦዲተር ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ማንኛውም ህብረት በአዋጁ ላይ የተመለከተውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር በመያዝ መደራጀት ያለበት ሲሆን የአባላቱ ቁጥር በሂደት እየሰፋ ሳይገደብ ሊቀጥል ይችላል፡፡
4. ህብረቶች ተባባሪና የክብር አባላት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ሆኖም እነዚህ አባላት ከህብረቱ ዓላማና ከአዋጁ መንፈስ ሳይወጡ ተስማሚና አዋጁን የማይቃረን አስተዋጽኦ ከማድረግ ያለፈ ሚና አይኖራቸውም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተባባሪና የክብር አባላትን የሚቀበል ህብረት የአባላቱን አይነትና የስም ዝርዝር እንዲሁም የተቀበለበትን ቀን በመግለጽ በየጊዜው ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
6. ተባባሪ እና የክብር አባላት በህብረቱ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት መብት ያላቸው ቢሆንም ድምጽ የመስጠትም ሆነ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አይኖራቸውም፡፡
7. ሁሉም መደበኛ የህብረቱ አባላት በጠቅላላ ጉባዔው ውስጥ እኩል ድምጽና ውክልና ይኖራቸዋል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ውክልና እንደየበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ህብረት ብዛት አንድና ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡

9. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ውክልና በጠቅላላ ጉባዔ ምርጫ ወይም ሁለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ብቻ የመሰረቱት ሲሆን የጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላቱን በስምምነት የሚወክሉ ይሆናል፡፡

10. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር ከአምስት ማነስ የለበትም፡፡ የቦርድ አባላት ከዚህ በላይ መጨመር እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ጊዜ ቦርዱን የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቁጥር ከቦርድ አባላት ቁጥር ሁለት እጥፍ እና ከዛ በላይ የበለጠ መሆን አለበት፡፡

## 9. ህብረት መመስረት ስለማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች

1. የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ህብረት መመስረት አይችሉም፡፡
2. የኢትዮጵያ ማህበራት ከኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበራት ጋር ህብረት መመስረት አይችሉም፡፡
3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከማህበራት ጋር ህብረት መመስረት አይችሉም፡፡

## 10. የህብረት ህብረት ስለሚመሰረትበት ሁኔታ

1. ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ህብረቶች የጋራ ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት የህብረት ህብረት ከመመስረት ውጭ ሌላ አማራጭ የሌላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ የህብረት ህብረት መመስረት ይችላሉ፡፡
2. በዚህ መመሪያ ስለ ህብረቶች አመሰራረት የተደነገጉት እንደ አግባብነቱ ለህብረት ህብረቶችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 11. የህብረት አቋም

1. ማንኛውም ህብረት የአባሎቹን ሥራ ለማስተባበር ወይም ለአባላት መብትና ጥቅም ብቻ የተቋቋመ ከሆነ እንደ ማህበር ሆኖ ይመዘገባል፡
2. በአዋጁና በደንቡ ስለ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የተደነገጉት እንደአግባብነቱ ለህብረቶችም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 12. መመስረት፤ መመዝገብና ውጤቱ

1. ማንኛውም ህብረት በተመሰረተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለምዝገባ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 65 ላይ የተመለከቱት የመመስረት ውጤቶች በተመሰረተ ህብረት ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. ማንኛውም ህብረት በኤጀንሲው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ህጋዊ ሰውነት ያገኛል፡፡

## 13. መሰረዝ፤መፍረስና ውጤቱ

1. በአዋጁ አንቀጽ 92-94 ስለ መሰረዝና መፍረስ የተደነገጉት ለህብረትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. ማንኛውም ህብረት የሚፈርሰው በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ቢሆንም ከጠቅላላ ጉባዔ ከ¾ኛ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ከዚያ በላይ ባልተገኙበት የሚወሰን የማፍረስ ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ማንኛውም ህብረት ሲፈርስ ንብረቱ ተመሳሳይ ዓላማ ላለው ህብረት እንዲተላለፍ ወይም በአባል በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት መካከል እንዲከፋፈል በህብረቱ የበላይ አካል ሊወሰን ይችላል፡፡ ቢሆንም ውሳኔው በኤጀንሲው ሳይጸድቅ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡

## 14. ድጋሚ ምዝገባን በተመለከተ

1. በነባሩ አሰራርና ህግ መሰረት በተለያዩ ስያሜዎች የተመዘገቡ ህብረቶች ይህ መመሪያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን የድጋሚ ምዝገባ ቅጽ በመውሰድና በዚህ መመሪያና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት አስፈላጊውን መስፈርቶች በማሟላትና ኤጀንሲው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በድጋሚ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ማንኛውም ህብረት ለድጋሚ ምዝገባ ሲቀርብ በህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ፣ የጠቅላላ ጉባኤው የተስማማበት ቃለ ጉባኤና የእያንዳንዱ የህብረቱ አባል ድርጅቶች በዳግም ምዝገባ የተሰጠው ሰርተፊኬት ከምዝገባ ቅጽና ሌሎች መስፈርቶችም ተሟልተው መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 15. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 16. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከጥር 15 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና**

**ማህበራት ኤጀንሲ**